# ፕሮፌሰሩ

ካፄው ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ጀምሮ
ጎጠኛውን ዘመን ከፋሽሽቱ አዳምሮ
ለሶስት አምባገነን አገዛዝ ጌታ አድሮ፣

ስንቱን ልሂቅ ምሁር ሰንቱን ወጣት ታጋይ
ስንቱን ያገር ተስፋ ስንቱን ባለ ራኢይ
ለሰየፈው ስለት ወዶ ገብ እጀታ
ፕሮፌሰሩ ነው አገሩን የፈታ።

ለአክሊሉ መረሸን የፍርድ ሂደት ሳያይ
ለአሰፋ ማሩ ሞት በጠራራ ፀሀይ
ፕሮፌሰሩ ነው የደም ዋጋ ከፋይ።

ለቀስተ ደመና በድንገት መጠንሰስ
ለቅንጅት መክሰም ለህብረቱ መፍረስ
ፕሮፌሰሩ ነው ቡራኬ ሰጪው ቄስ።

ኢትዮጵያን ለማድረግ የነፃነት ነዳይ
እንዳሸን ከፈላው የስለላ እንጉዳይ
ፕሮፌሰሩ ነው ትልቁ አገር ገዳይ።

ሚያዚያ 2007

አብርሃም በየነ